# *ዘላቂ ሰላም ኢትዮጵያ ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ ነው*

ከልጅነቴ ነፍስ ካወቅኩበት ከ1970ዎቹ ጊዜ ጀምሮ ስሰማ ያደግኩት እስካሁንም የሚሰማው በኢትዮጵያ፣ ሶማሊያ እና ሱዳን የአንድ አህጉር ልጆች ብሎም ከአንድ አብራክ የተገኙ ወንድማማቾች እና እህትቶማማቾች መካከል ትርጉም የለሽ እና አረመኔያዊ እርስ በርስ ግጭት እንደ ጠላት በመፈራረጅ ለእልቂት ተዳርገዋል።

በተመሳሳይ ጊዜ በአፍሪካ በኮንጎ ዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ፣በሴራሊዮን ፣ በላይቤሪያ፣ በሩዋንዳ፣ በቡሩንዲ፣ በአንጎላ እና በማሊ የእርስ በርስ ጦርነት ይካሄድ ነበር። በተጨማሪም በፍልስጤም፣ በኢራቅ፣ በኢራን፣ በእስራኤል፣ በፓኪስታን፣ በአፍጋኒስታን እና በካሽሚር የተደረጉ የጦርነት ድራማዎች በአለም አቀፍ ደረጃ በዜናዎች ላይ አዕምሯችንን የያዙ ነበሩ። አሁንም አንዳንዶቹ ሰላም ሲያገኙ ሌሎች ደግሞ ከጦርነት ክፉ አባዜ ወይም አዙሪት ለመውጣት ጥረት ያደርጋሉ ወይም አልቻሉም።

በኔ እምነት በየትኛውም መመዘኛ በ21ኛው ክፍለ ዘመን ምክንያታዊነት የጎደለው የእርስ በርስ ግጭት ወይም ፍጥጫ የትኛውም ወገን እንደ ጀግንነት ሊወሰድው አይችልም። ይልቁንም ጦርነት የኋላ ቀርነት እና የአስተሳሰብ መቀንጨር ማሳያ ነው።

ለዚህም ሁሌም እኔን የሚያሳስበኝ ነገር ቢኖር አንዳንድ ወገኖች በ12ኛው ክፍለ ዘመን ወይም ከዛ በፊት የነበሩትን ስልጣኔ፣የባህል ቱርፊት የግል አድርገው ሲከራከሩ እሰማለሁ። መከራከራቸው ባልከፋ ሆኖም እኔ የሚገባኝ ስልጣኔ እና ባህል በሰብዓዊነት ማማ ላይ የሚያስቀምጥ እንጂ እንደ አውሬ የሚያናክስ አይደለም። በቂም ትርክት በሌላ ወገን ላይ የሚያነሳሳ መሆንም የለበትም።

ለዚህም ነው በማለዳ ስለ አክሱምና የላሊበላ ሥልጣኔ እየፎከርክ ስትኩራራ ቆይተህ ረፋዱ ላይ ጠብ-መንጃ ይዘህ የገዛ ወንድሞችህን እና እህቶችህን ገድለህ መፎከር የቱ ላይ ነው ስልጣኔው? መግደልና መፎከር የከንቱ ከንቱነትና የኋላ ቀርነት መገለጫነቱን መረዳት እንዴት ያዳግታል።

ለማንኛውም ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ቅሬታ ሊፈታ የሚችለው በውይይት እና በውይይት ብቻ ነው። እንደዚያ ማድረግ ካልተቻለም በሀገር ውስጥ፣ በአህጉራዊ እና በአለም አቀፍ ደረጃ በሰፊው ተደራሽ የሆነውን የህግ የበላይነት መከራከር ወይም መደራደር ይቻላል። ሆኖም እርግጥ ነው እንደዚህ ያለ ባህል እንዳይዳብር ያለፉት አርባ አመታት አገዛዞች ሁሉን በር ዝግ በማድርጋቸው በጠብ-መንጃ ብቻ እንድናሰብ መሆናችን እጅግ የሚያሳዝን ነው። ለዚህ ተጠያቂ አንድ አካል ብቻ ስለማይሆን ጣት ከመቀሰር መቆጠብ አስፈላጊ ነው።

በአፍሪካ ውስጥ አብዛኛው ግጭቶች የሚደገፉት በክፉ ዓላማ ጠንሳሾች የውጭ ኃይሎች እና በልሂቃን ጥምር ዝግጅት ነው። ይህም አህጉራዊ እና ዓለም አቀፋዊ ኃይሎች ከእንደዚህ ዓይነት አረመኔያዊ ጦርነቶች ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ትርፍ ለማግኘት በሚፈልጉ ቡድኖች እንደሆነ የታወቀ ነው።

ይሁን እንጂ የፖለቲካ እና የኢኮኖሚ ጥቅም ያላቸው ልሂቃን የእነዚህን ግጭቶች እሳት በማባባስ የሚጫወቱት ሚና እጅጉኑ ከፍተኛ መሆኑን ማወቅ አስፈላጊ ነው። ከአገር ውስጥ ልሂቃን ድጋፍ እና ጥቅም ውጭ የሆኑ የውጭ ኃይሎች ለጥቅማቸው ሲሉ የአገር ውስጥ ፖለቲካን መበዝበዝና ማቀጣጠል የሚችሉበት እድል ውስን ነው።

ይህ በእንዲህ እንዳለ በኢትዮጵያ፣ በሶማሊያ እና በሱዳን በተደረጉ ጦርነቶች በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች በስደታት ከቄያቸው አፈናቅለዋል፣ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩት ተገድለዋል፣ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ደግሞ በስነ ልቦና ስሜት ተጎድተዋል። እነዚህ በወንድማማቾች እና እህትማማቾች መካከል የተካሄደው ዘግናኝ ጦርነት ሁለት አዳዲስ ሀገራት ማለትም ኤርትራ እና ደቡብ ሱዳን እንዲፈጠሩ ምክንያት ሆኗል፣ብሎም ሶማሊያ ወደ ትንንሽ የመንደር መንግስታት እንድትከፋፈል አድርገዋል።

በአፍሪካ ቀንድ ዘላቂ ሰላም ለማምጣት ያለውን ውስብስብ ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባት በኢትዮጵያ ስላለው ግጭት ተጨባጭ ዕውቀትና ልምድ መሠረት ያደረገ ውይይት ማድረግ አስፈላጊ ነው። የኢትዮጵያ የእርስ በርስ ጦርነት በአራት ዋና ዋና ምክንያቶች እንደሚቆራኝ እምነቴ ነው። እነዚህም የአድዋ ድል መዘዝ፣ በውሃ ፖለቲካ፣የተሳሳተ የፖለቲካ ርዕዮተ ዓለም እና የጂኦፖለቲካዊ ምክንያቶች ናቸው። ያለምንም ፍርሃትና ወገንተኝነት በምክንያታዊነት ምክንያቶቹን መተንተን አስፈላጊ ቢሆንም፣ ነገር ግን ካለው የጋዜጣው ውስን ቦታ የተነሳ፣ ወሳኝ የሆኑትን የፖለቲካ እና የአስተዳደር ጉዳዮችን በመመርመር ላይ አተኩራለሁ።

በመጀመሪያ ከብዙዎቹ አንደኛው ምክንያት የኢትዮጵያዊ ፖለቲካ ጡዘት የሚጀምረው "እኛ እና እነሱ" ከሚል ግልብ አመለካከትና የመንጋ አስተሳሰብ ነው። ይህን መሰረት አድርገን በሰሜኑ አገራችን አሁን ያለው ጦርነት ለምን እንደቀጠለ፣ በሺዎች የሚቆጠሩ ወጣቶችን ህይወት እየቀጠፈ ሴቶችና ህጻናትን በጦርነት ቀጣና እያፈናቀለ እስከመቼ እንደሚቀጥል መጠየቅ አስፈላጊ ነው። ጥያቄው ሰላምን ፈላጊነታችንን መግለፅ እና ማስረፅ የምንችለው እንዴት ነው? የአፍሪካ ቀንድ በውስጥ ግጭቶች በተለያዩ አይነት ሁሉን አቀፍ ጦርነት እየተናጠ ባለበት በአሁኑ ወቅት ስልታዊ የሆነ አድሎአዊነት እና ከታሪካዊ ጠላቶቹ የሚሰጠው ድጋፍ ተባብሶ ቀጥሏል። ይኸንንም ሁኔታ ጣት ከመቀሰር ባለፈ መልክ እንዴት ሰላምን ማስፈን እንችላለን የሚለውን ለመመለስ ብሎም ግንዛቤያችንን የማስፋት የሚደረግ ጥረት አንዱ አካል ነው።

ሰላምን መፈለግ የጋራ ውድቀትን በጥልቀት መመርመር እና የተሳሳተውን አመለካከት፣እብሪተኝነት፣ ጎጠኝነት (ego) መመርመር አስፈላጊ ነው። ስለዚህም አንዱ ወይም ሁለቱም ወገኖች የሚዋጉት ረብ የሌለው ጦርነት መሆኑን ተገንዝበው እራሳቸውን እንዲገመግሙ፣ሰብአዊነት እንዲኖራቸው እና እራሳቸውን እንዲጠይቁ በማሰብ መሰረታዊ ጥያቄዎችን ከወገንተኝነት በነፃ መልኩ ማንሳት እፈልጋለሁ።

የጥያቄው ቅድመ ተከተል ምንም አይነት ምክንያት የለውም።

<u>ለሕዝባዊ ወያነ ሓርነት ትግራይ (ህወሓት)፡-</u>

ከ1935 ዓ.ም የመጀመሪያው ቀዳማይ ወያነ እንቅስቃሴ ጀምሮ በህወሀት የቀጠለው በኢትዮጵያ ውስጥ ጉልህ የሆነ የአመፅ እና የብጥብጥ ምንጭ ሆኖ ከሁለቱም ወገኖች በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎችን ህይወት ቀጥፏል። በዚህም የተነሳ ንፁሀን የትግራይ ወጣቶች ለጥቂት የልሂቃን ቡድን በስልጣን ላይ እንዲቆይ ለማድረግ ኢ-ፍትሃዊ በሆነ የበላይነት ስካር ማስፈጸሚያ መሳሪያ ሆኖ ቆይቷል።

ለህወሀት መሪዎች መጠየቅ የሚፈለገው መቼ እና ምን ያህል ሰዉ ሲሞት ነው የህዝብ በገፍ ሞት የእርስ በእርስ እልቂት ኣሳዝናኖቸሁ ወደ ልቦናችሁ የምትመለሱት? መቼ ነው የጋራ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን በውይይትና በሰለጠነ አግባብ መፍታት የምትለምዱት?

ከ1993 እስከ 2010 እንደ ገዥ ፓርቲ እና መንግስት በቆያችሁበት ጊዜ፣ ትሰቡኩ የነበረው የተጨቆኑና የተገለሉ ድምፆችን የጎሳ እና የአናሳ የጎሳዎች (ethnic and tribal minorities) ተቆርቋሪ ወይም

*ሻምፒዮን ነን ትሉ ነበር። ይሁንና በአንፃሩ ከናንተ ጋር ተመሳሳይ የጎሣ አወቃቀር የነበራቸውን እንደ ኦሮሞ ነፃነት ግንባር (ኦነግ)፣ ኦጋዴን ብሄራዊ ነፃ አውጭ ግንባር (ኦብነግ)፣ ጋምቤላ እና ቤንሻንጉል ያሉ የተቃዋሚ ቡድኖችን ጨምሮ ሁሉንም አይነት ተቃዋሚዎች ለማጥፋት ትንቀሳቀሱ ነበር። በተጨማሪም ከፅበኝነት ባህሪያችሁ የመነጨ ከኤርትራ ጋር የድንበር ግጭት ውስጥ አገሪቱዋን አስገባችሁ፣ በሶማሊያ የውስጥ ጉዳይ በመግባት አገሪቱዋን በጠላትነት አስፈረጃችሁ፣ ወደ ግማሽ ሚሊዮን የሚጠጉ የኢትዮጵያ ወታደሮችን አፈናቅላችኋል፣ እና በአጠቃላይ ተቃዋሚዎችን ማሳደደና ማጥፋት ተግባራችሁ ነበር።*

*ለምን ይሆን በስልጣን ዘመናችሁ ለጦርነት ትዘጋጁ የነበረው? ይህንን ያህል መሳሪያ በኢትዮጲያ ህዝብ አንጡራ ሀብት ገዝታችሁ እንደ ጃርት እየቆፈራችሁ የቀረባችሁት? ይህ ለኢትዮጵያ ሰላም እንደማይሆን እሙን ነው። አሊያም ለዘላለማዊ ስልጣን ወይስ ለቅዠት ሪፐብሊክ? እኔ እንደ አንድ አፍቃሪ አፍሪካዊ* (Pan Africanist) *አመለካከት አይደለም የትግራይ ክ/ሀገር ኢትዮጵያም ብሔር የሚለውን ጽንሰ-ሐሳብ በአንጻራዊነት አታሚላም።*

*የመርሳት አባዜ ከሌለባችሁ በስተቀር ከ28 አመታት ጨቋኝ አገዛዝ በኋላ ከማዕከላዊ መንግስት ሥልጣን የተባረራችሁት በገዛ ጓዶቻችሁ መሆኑን የምታውቁ ይመስለኛል። ለምን ታዲያ መላውን የኢትዮጵያ ህዝብ በጠላትነት ፈረጃችሁ የእልቂት ድግስ የደገሳችሁለት? ይህ ምን አይነት እብደት ነው?*

***ለገዥው ብልፅግና ፓርቲ እና ለኢትዮጵያ መንግስት፡-***

*የህወሃትን ሕገ መንግሥት ተቀብሎ እያስፈጸሙ እና እየተከላከሉ የህወሃትን መዋቅር መታገል ተቃርኖ አይደለምን? መንግስት በስታሊናዊ የብሄር እና ብሄረሰቦች ጥያቄ ላይ የተመሰረተውን ህገ መንግስት ለማስተካከል ዝግጁ የሚሆነው መቼ ነው? መንግስት ሀገሪቱን በቋንቋ እና በጎሳ ላይ የተመሰረተውን የአስተዳደር መዋቅር የሚያርመው መቼና እንዴት ነው?*

*መንግስት የጨቋኝ እና ተጨቋኝ የሚለውን የተሳሳቱ ትርክቶችን ማስተካከል በመንግሥት ደረጃ ተቋማዊ በሆነ መልኩ የሚጀምረው መቼና እንዴት ነው? ሁሉም ኢትዮጵያዊ ህዝብ የጥቁር* (Negroid) *ዘር ሆኖ ሳለ የጎሳዎችን እና የቋንቋ ልዩነት የዘር እንደሆነ ተደርጎ የሚቀርበው መቼ ነው ለማቆም ጥረት የሚደረገው?*

*የትግራይን ህዝብ እና ህወሀትን አንድ አድርጎ ማቅረብ እጅጉን ስህተት ነው። አንድ ሊሆኑ ስለማይችሉ፣ ሆኖም ከህወሀት ጨቋኝ ባህሪ በመነሳት ህዝቡን አስገድዶ በማሳመን ከጎኑ ሊያሰልፍ እንደሚችል እሙን ነው። ሆኖም መንግስት እንደ መንግስትነት ይህንን እውነታ ለመለወጥ ምን አይነት የሰላም አማራጮች አሉት?*

*የሰላሙ ሃሳቦችም ወጥነት ባለው መልኩ ለሁሉም ኢትዮጵያውያን መገለጽ የለባችሁም ወይ? መንግስት ለትግራይ ክ/ሀገር ሁሉንም አስፈላጊ አገልግሎቶች ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ የመስጠት ግዴታ አለበት። ለዚህ ምን ዓይነት ጥረቶችን ነው የሚያደርገው? ይህም የመንግስት ጉዳይ ብቻ ሳይሆን የህዝብም ጥያቄ መሆን አለበት።*

***ለትግራይ ክ/ሐገር ህዝብ፡-***

*መቼ ነው የትግራይ ህዝብ ህወሓት በሌላው ኢትዮጵያዊያን ወንድሞቻቸው እና እህቶቻቸው ላይ የሚያደርሰውን ግፍ በቃ ብለው ስለ ሰላም የሚጠይቁት?*

መቼ ነው የትግራይ ህዝብ የሰላም አየር እንዲተነፍስ ከሌሎች ወንድሞቻቸው እና እህቶቻቸው ጋር በሰላም ከሌላው የኢትዮጵያ ክፍል ጋር ተስማምተው እንዲኖሩ ህወሓት ሆነ በማእከላዊ መንግስትን የሚጠይቁት?

የትግራይ ክ/ሀገር ህዝብ የኢትዮጵያን ባህልና ወግ በሚመጥን መልኩ እና በሰለጠነ አግባብ በማእከላዊ መንግስት ላይ ያለውን ስጋት እንዲያሰማ ጫና እንዲያሣድር እማፀናለሁ።

## ለኢትዮጵያ ህዝብ፡-

ኢትዮጵያ "የሰው ልጅ መገኛ" እንዲሁም ከጥቂቶች አንደኛዋ የጥንት ሥልጣኔ ማዕከል ተብላ ትታወቃለች። ለአፍሪካ እና ለዓለም ብዙ የፍልስፍና ጥበብ ምንጭ በመሆን አስተዋጽኦ አድርጋለች። ኃያላን ቅኝ ገዢዎችን በማሸነፍ ለመላው ጥቁር ህዝብ ብሎም ለአፍሪካውያን ኩራት ነው። በእነዚህ ገድሎች ውስጥ የትግራይ ክ/ሀገር ህዝብ ያደረገዉ አስተዋጾ እጅግ ከፍተኛ ነው። በመሆኑም ተገቢ ክብር እና እውቅና ያሻዋል።

ስለሆነም የተቀረው የኢትዮጵያ ዜጎች የትግራይን ህዝብ ከማግለል እንዲቆጠቡ ብሎም "እኛ" እና "እነሱ" ከሚል እኩይ አመለካከት እንዲወጡ አስፈላጊ ነው። ይህ ማለት ሁሉን ኢትዮጵያዊ አይወክልም። እኛ "እነሱን ነን" "እነሱ" በውስጣችን ነው የሚኖሩት ስለዚህ "እኛና" እነርሱ" የሚባል ነገር ሊኖር አይገባም።

ስለዚህ መቼ ነው የኢትዮጵያ ህዝብ በትግራይ ክ/ሀገር ህዝብ ላሉት ወንድሞቹ እና እህቶቹ ላይ የሚያደርሰውን ግፍ በቃ ብለው ከጦርነት አማራጭ ውጪ በሰላም የሚፈታበትን አግባብ መንግስትን የሚጠይቁት?

## ለአለም አቀፍ ማህበረሰቦች፡-

እንደ አንድ አፍሪካዊ እና ኢትዮጵያዊ፣ ከእውነተኛ ተቆርቋሪነት የተነሳ እጃቸውን የዘረጉትን አደንቃለሁ። ይሁን እንጂ በሰሜናዊ ኢትዮጵያ ውስጥ በተፈጠረው ግጭት ውስጥ የሚመለከታቸው ሁሉም አካላት ኢትዮጵያዊ መፍትሄን ማበረታታት ይመረጣል።

## ለአፍሪካ ህብረት፡-

የአፍሪካ ህብረት በሁለቱም ወገኖች ላይ ያለ አድልዎ የመሳተፍ እና አስፈላጊውን የሰላም አማራጮች የማቅረብና የማደራደር ሙሉ ህጋዊ እና ሞራላዊ መብት አለው። ሆኖም የውጭ ሃይሎችን ጣልቃ ገብነት መቃወም ይጠበቅበታል እና የሰላም መፍትሄው አፍሪካዊ መሆን አለበት። ያለበለዚያ ታሪክ ይፋረዳችኋል።

## ለአፍሪካ ምሁራን፡-

በኢትዮጵያ መንግስት እና በህወሀት ታጣቂዎች መካከል ያለውን ትግል የሚመለከቱ በርካታ ህትመቶችን ለማየት እና ለማጥናት እድሉን አግኝቻለሁ። አንዳንዶቹ በእኔ እምነት የፕሮፓጋንዳ ሰለባዎች ናቸዉ። አንዳንድ የሁኔታው መሰረታዊ እውቀት የሌላቸው ምሁራን በፍልስጤም እና በእስራኤል ወይም በዩክሬን

እና በሩሲያ መካከል ባለው አይነት ግጭት አስመሰለው አቅርበዋል። ስለሆነም ነባራዊውን ሁኔታ ለመረዳት ጥልቅ ጥናትና ምርምር ማካሄድ የትኛውንም ወገን ሳይደግፉ ገለልተኛ አመለካከት እንዲይዙ እመክራለሁ ተመራጭም ነው።

ምክንያቱም ዛሬ በውሸት መነሻነት የምንጽፈው ማንኛውም አስተያየት ለአፍሪካ አንድነት፣ ሰላምና ልማትን በረዥም ጊዜ ውስጥ መጥፎ አርአያ በመሆን እኛኑ ይጎዳናልና።

<u>**የመፍትሔ ሃሳብ:**</u>

ይህ የእርስ በእርስ ግጭት በጦርነትም ሆነ በሰላማዊ ድርድር ቢፈታም ዘላቂያዊ ዋስትና ሊሆን አይችልም። ዘላቂያዊ ሰላማዊ ዋስትና በህዝቦች መካከል የሚደረግ መተማመን፣መግባባት እና ለላቀ አላማ በጋራ መቆም ይጠይቃል። ስለሆነም ከዚህ በታች ያሉት ሁለት ዋና ዋና ሃሳቦች መንግስትም ሆነ አማጺያኑ ቢገነዘቡት መልካም የሰላም አማራጭ ያመጣል ብዬ አምናለሁ።

፩ኛ: "የኢትዮጵያን ችግር በኢትዮጵያውያን" በሚል ጽንሰ ሀሳብ ከመላው ኢትዮጵያ የተውጣጣ የአዋቂዎችና የሽማግሌዎች አገርአቀፍ ተግባራዊ ኮሚቴ በማዋቀር በጦርነት የተጎዳውን ብሎም ጦርነት የሚካሄድበትን አካባቢ ያለውን ህዝብ በማናገር ሰላም የሚሰፍንበት መንገድ መቀየስ ይሆናል።

፪ኛ: ሰላም እንዲሰፍን አስተዳደራዊ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎችን በህዝብ ፍቃድ ይሉኝታ ማግኘት አስፈላጊ ነው። ስለሆነም በሀቀኝነትና ያለምንም ወገንተኝነት አስተዳደራዊ ድንበሮችን በህዝብ ፍላጎትና በሳይንሳዊ ዘዴ በመታገዝ መፍታት አስፈላጊ ነው። ከዚህም በተጨማሪ ከፍተኛ የጦር መሳሪያ ክምችት ከአካባቢው ማስወገድ በህዝብ የሚሰራ ተግባር እንዲሆን ይገባል።

ማስታወሻ: ይህ ጽንሰ ሀሳብ አሁን ካለው አገር አቀፍ የእርቅና የሰላም ኮሚሽን የሚገናኝ ሳይሆን ውስን ኃላፊነት ኖሮት የጦርነት አዝማሚያዎችን የሚቀለብስና ዘላቂ ሰላምን የሚያመጣ ሆኖ ቢታይ መልካም ነው። ሆኖም ድምር ውጤቱ የአገር አቀፍ የእርቅና የሰላም ኮሚሽን የሚረዳ ይሆናል።

በመጨረሻም ሁለቱም ወገኖች የተሳሳተውን አመለካከት፣እብሪተኝነት፣ ጎጠኝነት (ego) ወደ ጎን በመተው የሰለጠነ መፍትሄ እንዲፈልጉ አጥብቄ አማጸንሃለሁ። በዚህም የኢትዮጵያን የግጭት ዘመን ያበቃል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ።

ለ2015 አዲስ አመት የሰላም አየር የሚንተነፍስበት አመት እንዲሆን ለመላው ኢትዮጵያ ህዝብ እመኛለሁ። ይህ ትርጉም የለሽ እና አረመኔያዊ ጦርነት ከኋላችን ትተን እና አገራችን ተረጋግቶ በሰላም እና ብልጽግናን እንደምትቀጥል ተስፋዬ ሙሉ ነው።

<u>**የፅሁፉ አበርካች፡-**</u> *ዶ/ር ሰይፈ ታደለ ኪዳኔ፣ በጆሃንስበርግ ዩኒቨርሲቲ የፓን አፍሪካዊ አስተሳሰብ እና ውይይት ተቋም (አይ-ፒ-ኤ-ቲ-ሲ) ከፍተኛ የምርምር ባልደረባ ፣ እና የአፍሪካ ድምጽ ፕሬዚዳንት (President of Africa Speaks): with Special Consultative Status at the United Nations ECOSOC*